ይህ ሰነድ በHUD የወጣው ሕጋዊ ሰነድ ትርጉም ነው። HUD ይህንን ትርጉም ያዘጋጀልዎ መብትና ግዴታዎን በቀላሉ እንዲያውቁ እርስዎን ለመርዳት በማሰብ ብቻ ነው። የዚህ ሰነድ ኦፊሴላዊ፣ ሕጋዊና ገዥ ቅጂ በእንግሊዝኛ የተዘጋጀው ይሆናል። ይህ የተተረጎመው ሰነድ ኦፊሴላዊ ሰነድ ሆኖ አያገለግልም።

**ዓመጽ፣ በተቃራኒ ጾታ ጓደኛ የሚፈጸም ዓመጽ ወይም ትንኮሳ**

**የዩኤስ የቤቶችና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት**
የቤቶች ጉዳይ ቢሮ

OMB Approval No. 2502-0204
Exp. 05/31/2011

# የኪራይ ውል ተጨማሪ ክፍል

## <u>በሴቶች ላይ የሚፈጸም ዓመጽና የፍትሕ ዲፓርትመንት የማሻሻያ ደንብ 2005</u>

| አከራይ | ተከራይ | የዩኒት ቁ. እና አድራሻ |
|---|---|---|
| | | |

ይህ የኪራይ ውል ማሻሻያ ከላይ በተጠቀሱት ተከራይና አከራይ መካከል የተፈጸመው ውል ላይ የሚከተሉትን አንቀጾች የሚጨምር ይሆናል፦

### የተጨማሪ ክፍሉ ዓላማ

ከላይ የተጠቀሰውን የዩኒት ቁጥር በተመለከተ የተደረገው ኪራይ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ዓመጽና የፍትሕ ዲፓርትመንትን የማሻሻያ ደንብ 2005 (Violence Against Women and Justice Department Reauthorization Act of 2005 (VAWA)) እንዲያካትት ተደርጎ ተስተካክሏል።

### ከሌሎች የኪራይ ውሉ ድንጋጌዎች ጋር የሚፈጠር ግጭት

በዚህ ተጨማሪ ክፍል እና በውሉ ሌሎች ክፍሎች ድንጋጌዎች መካከል ማንኛውም ዓይነት ግጭት ቢፈጠር የዚህ ተጨማሪ ክፍል ድንጋጌዎች የጸኑ ይሆናሉ።

### የኪራይ ውሉ ተጨማሪ ክፍል የአገልግሎት ጊዜ

ይህ የኪራይ ውል ተጨማሪ ክፍል ተፈጻሚ የሚሆነው ከ _______________ አንስቶ ይሆናል። ይህ የኪራይ ውል ተጨማሪ ክፍል የኪራይ ውሉ እስከሚያበቃበት ጊዜ ድረስ ተግባራዊነቱ የጸና ይሆናል።

### የVAWA ከለላዎች

1. አከራዩ የቤት ውስጥ ዓመጽን፣ በተቃራኒ ጾታ ጓደኛ የሚፈጸምን ዓመጽ ወይም ትንኮሳን እንደ ከባድ ወይም ተደጋጋሚ የኪራይ ውል ጥሰት አይቆጥረውም፤ ወይም ለጥቃቱ ሰለባ የሚሰጠውን እገዛ፣ ኪራዩን ወይም የተከራይ መብቱን ለማቋረጥ እንደ “በቂ ምክንያት” አይወስደውም።
2. አከራዩ፣ የጥቃቱ ሰለባ የሆነው ወይም ዛቻ የደረሰበት ተከራዩ ራሱ ወይም የተከራዩ የቅርብ ቤተሰብ በሚሆንበት ጊዜ ከተከራዩ የቤተሰብ አባል አንዱ ወይም ማንኛውም በተከራዩ ቁጥጥር ስር ያለ እንግዳ ወይም ሌላ ሰው የሚፈጽመውን ከጥቃት ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅነት ያለው የወንጀል ድርጊት ለተከራዩ የሚሰጠውን እገዛ፣ ኪራዩን ወይም የተጠቃሚነት መብቱን ለማቋረጥ እንደ ምክንያት አድርጎ አይቆጥረውም።
3. በVAWA መሠረት የህግ ከለላ ማግኘት ይቻል ዘንድ አከራዩ ጥቃት የደረሰበት ግለሰብ ራሱ ወይም የቤተሰብ አባሉ ስለ ተበዳዩ በመሆን ግለሰቡ የጥቃት ሰለባ እንደሆነ እንዲያረጋግጥና የቤት ውስጥ ዓመጽ፣ በተቃራኒ ጾታ ጓደኛ የሚፈጸም ዓመጽ ወይም ትንኮሳ ማረጋገጫ ቅጽ HUD-91066 (Certification of Domestic Violence, Dating Violence or Stalking, Form HUD-91066) ወይም በማረጋገጫ ቅጹ ላይ የተመለከቱ ሌሎች ሰነዶችን ሞልተው በ14 የሥራ ቀናት ወይም በጋራ ስምምነት በሚሰጠው የማራዘሚያ ጊዜ ውስጥ እንዲልኩ በጽሑፍ ይጠይቃል። በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማረጋገጫውን ወይም ተጨማሪ ማስረጃ የሚሆኑትን ሰነዶች ሳያቀርቡ መቅረት እንዲባረሩ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

| የፊርማው ቦታ ጠፍቷል |
|---|